# የታወቁ የንግድ ምልክቶች ጥበቃ ላይ
# ትምህርታዊ ውይይት

## ዋቤ ሸበሌ ሆቴል

ሰኔ 17 ቀን 2009 ዓ.ም.

- የስብሳበው አጀንዳ/ርዕሰ-ጉዳይ፡ የታወቁ የንግድ ምልክቶች ጥበቃ ላይ ትምህርታዊ ውይይት
- ጽሑፍ አቅራቢ፡- ወ/ሮ ልደት አበበ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ
- አወያይ፡- አቶ ቢኒያም ታፈሠ - የአ/አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግና አስተዳደር ኮሌጅ መምህር
- የስብሰባው ቦታ፡- ዋቤ ሸበሌ ሆቴል
- በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ፡- ጠበቆች፣ የማኅበሩ አባላትና ሌሎችም
- የአውደጥናቱ ቀን፡- ሰኔ 17 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 7፡00 ሠዓት

## <u>አቶ አበራ ኃ/ማርያም - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ተ/ ዋና ዳይሬክተር</u>

የማኅበሩ ተ/ዋና ዳይሬክተር የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከተለያዩ የሕግ ባለሙያዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ በመፍጠር እና ሥነ-ሕግን በማሳደግ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የዕለቱ የውይይት ርዕስ የታወቁ የንግድ ምልክቶች ላይ ትምህርታዊ ውይይት የምናደርግ ሲሆን ከፕሮጀክተር አለመስራት ጋር ተያይዞ ለደረሰው መስተጓጎልና መዘገየት በማኅበሩና በራሳቸው ስም ይቅርታ በመጠየቅ የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በውይይቱ ላይ የተገኙ ባለሙያዎችን በማመስገን እና የዕለቱ ውይይት የተሳካ እንዲሆን በመመኘት የስብሰባውን በይፋ መከፈት አብስረዋል፡፡

## <u>አቶ ቢኒያም ታፈሠ - አወያይ</u>

አወያዩ አቶ ቢኒያም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ካስተላለፉ በኋላ የጽሑፍ አቅራቢዋን የወ/ሮ ልደት አበበን የግል ፕሮፋይል አቅርበው የእለቱ አጀንዳ በታዋቂ የንግድ ምልክቶች ላይ የሚደረግ ትምህርታዊ ውይይት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ታዋቂ ወይም ዝነኛ የንግድ ምልክቶች ከሕጉ አንፃር እንዲሁም በተግባር የሚታዩ ሁኔታዎችን ጭምር በሚዳስስ መልኩ ጽሑፉ የሚቀርብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

እውቅና በአለምአቀፍ ደረጃ ወይም ከባባዊ ሁኔታ ሊኖረው እንደሚችል የጠቆሙት አወያዩ ታዋቂ የንግድ ምልክቶች ላይ ውይይት የማድረግ ጠቀሜታ በዋናነት እነዚህ ምልክቶች ከተራ

ምልክቶች በአብዛኛው ሰዎች ያላግባብ በመጠቀም abuse የመደረግ ተጋላጭነታቸው ከፍተኛ በመሆኑ እንደሆነ በመግለፅ ከኢኮኖሚ እድገት ጋር ተያይዞ በinvestment ላይ የሚኖረው implication ቀላል አይሆንም ብለዋል፡፡ በትምህርታዊ ውይይቱ ላይ ጉዳዩን የሚመለከቱ ሕጎች ምሳሌ ሊሆኑ ከሚችሉ ኬዞች ጋር ማንሳት ለውይይቱ የላቀ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው በመጥቀስ መድረኩን ለጽሑፍ አቅራቢዋ ወ/ሮ ልደት አበበ አስረክበዋል፡፡

<u>ወ/ሮ ልደት አበበ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

አወያዩን አመስግነው ያለpower point ጽሑፉን ማቅረብ እጅግ አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልፀው የዕለቱ የመወያያ አርዕስት ዝነኛ የንግድ ምልክቶች ላይ ሲሆን ከሌሎች ተራ ምልክቶች ጋር ሲነፃጸር ለታዋቂ ምልክቶች የተለየ ጥበቃ የሚቸራቸው መሆኑን ገልፀው በታዳጊ ሀገራት ለአእምሯዊ ንብረት መብቶች የሚሰጠው ከለላ እና ጥበቃ ዝቅተኛ እንደሆነ አስቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ intercontinental hotel በአሜሪካ ውስት የሚገኝ የሆቴል ንግድ ሠንሠለት መሆኑን ነገር ግን በዕኛ ሀገር ያለው locally operate ሚያደርግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



የሀገራችን ሕግ ለንግድ ምልክት ትርጓሜ የሠጠ ሲሆን እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

*"የንግድ ምልክት" ማለት የአንድን ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱ ቃላቶችን፣ ምልክቶችን፣ ዲዛይኖችን፣*

*ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን ወይም የዕቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርፅ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡*

በሚል የንግድ ምልክትና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 501/1998 ያስቀምጣል፡፡

በሀገራችን ወደ 15,000 የሚጠጉ የንግድ ምልክቶች ተመዝግበው እንደሚገኙ የጠቆሙት ጽሑፍ አቅራቢ የንግድ ምልክት ጥበቃ በሁለት መንገድ ሊገኝ የሚችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በመርህ ደረጃ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚገኘው በምዝገባ ይሁን እንጂ አለማስመዝገብ ከመጠቀም አያግድም ብለዋል፡፡ ለረዥም ጊዜ በመጠቀም ጥበቃ የሚገኝበት ልማድ አለ፡፡ የአምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የንግድ ምልክትን ሲመዘግብ በቅድሚያ ባለምርቱ ማመልከቻ ይዞ ይመጣል ከዚያም በሕጉ መሠረት ከሞራል እና ከሕግ አለመቃረኑ ይታያል፡፡ ከዚያም በምልክቱ ላይ ተቃውሞ ያላቸው ሰዎች ካሉ መብታቸውን እንዲጠቀሙ በጋዜጣ ላይ ይወጣል ብለዋል፡፡ ለምሳሌ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የንግድ ምልክት ለመመዝገብ በማመልከቻ ጠይቆ ፅ/ቤቱም ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ ለተቃውሞ በጋዜጣ ወጥቶ ሳለ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ቅሬታውን ያቀረበ በመሆኑ ሳይመዘገብ ቀርቷል፡፡

የንግድ ምልክት በጥቁር እና ነጭ አሊያም በከለር ሊሆን እንደሚችል ገልፀው የምልክቱን ልዩ ባህርይ የሚቀንስ ወይም የሌላውን መብት የሚጥስ እስካልሆነ ድረስ ጥበቃ ሊደረግላቸው የማይችሉ ክፍሎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ የንግድ ምልክት ከምርቱ ውጭ የሆነ የተለየ ቃል፣ ቅርፅ ወዘተ ማለትም distinctive መሆን አለበት ብለዋል፡፡ ለምሳሌ apple ፍራፍሬ ሲሆን ነገር ግን በንግድ ምልክትነት የሚታወቀው በኮምፒውተር እና ስልኮች ነው፡፡



ለብዙ ዓመታት ጥቅም ላይ በመዋል ታዋቂና ዝነኛ የሆኑ የንግድ ምልክቶች ያሉ ሲሆን ለነዚህ ምልክቶች የተለየ ጥበቃ ይሰጣል፡፡ የንግድ ምልክት ጥበቃ መብት ሞኖፖሊን የሚያጎናፅፉ በመሆኑ ተመሳሳይ የንግድ ምልክት ተመዝግቦ ጥበቃ አይሰጥም ብለዋል፡፡ ቀደም ብሎ

የተመዘገብ ምልክትን የሚጠቀም ሰው የቀዳሚ አስመዝጋቢውን መብት ጥሷል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ “apple” ከሚለው ቃል ላይ “e” በማስቀረት “appl” በሚል መመዝገብ አይችልም በማለት በምሳሌ ያስረዱ ሲሆን ምዝገባው የሚከለከልበት ዋነኛው ምክንያት ተጠቃሚውን ካላስፈላጊ መሳከር እና መደናገር ጥበቃ ለመስጠት እና ለቀዳሚ አስመዝጋቢ ምርትና አገልግሎት ጥበቃ ለመስጠት ጭምር ነው በማለት አብራርተዋል፡፡



እጅግ ታዋቂ የሆኑ የንግድ ምልክቶች በማመሳሰል መሳከር ወይም መደናገርን ይፈጥራል በሚል ምክንያት ከምዝገባ የሚከለከለው በአዲስ ሊመዘገብ የመጣው አመልካች የሚያመርተው ምርት ዓይነት ተመሣሣይ ሲሆን ነው ብለዋል፡፡ ለምሳሌ apple የሚታወቀው ለኮምፒውተር እና ለሥልኮች በመሆኑ ቻፒስቲክ ለማምረት apple በሚል የንግድ ምልክት ቢመጣ መደናገር ይፈጥራል ማለት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዓይነት ሁኔታ በተግባር እየበዛ መጥቷል ብለዋል፡፡ ሌላው በመርቸንዳይዝ ዕቃዎችን የሚያመርቱ የንግድ ምልክቶች ሲሆኑ እነዚህ ተቋማት ብዙ ዓይነት ዕቃዎችን በአንድ የንግድ ምልክት ይነግዳሉ ለምሳሌ ironman፣ spiderman፣ superman ወዘተ የሚባሉ ከሕፃናት ልብሶችና መጫወቻዎች ጀምሮ ብዙ ምርትን በተመሳሳይ ምልክት ለገበያ ያቀርባሉ፡፡

 

የፓሪስ ኮንቬንሽን ከ1920ዎች ጀምሮ ተግባራዊ መደገረግ የተጀመረ ሲሆን የኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት ምንም እንኳ በሀጋራቸው ያልተመዘገበ ቢሆንም ታዋቂ በመሆኑ ብቻ ጥበቃ ይቸረዋል፡፡ ቀደም ብሎ ለምርቶች ብቻ ጥበቃ ሲሰጥ የነበረ ይሁን እንጂ በTRIPS Agreement መሠረት አገልግሎቶች እንዲጨመር ተደርጓል፡፡ ለምሳሌ Mcdonald ታዋቂ የአገልግሎት ምልክት ነው፡፡

አንድ የንግድ ምልክት ታዋቂ ወይም ዝነኛ የሚባለው ምን ሲሆን ነው የሚለውን ጥያቄ ያነሱት ጽሑፍ አቅራቢዋ TRIPS ወይም የፓሪስ ስምምነት ይህን ጥያቄ የማይመልሱ መሆናቸውን ገልፀው አንድ የንግድ ምልክት ታዋቂ ነው አይደለም የሚለውን በተመለከተ በአባል ሀገራት እንዲተዳደር የተተወ ነው በማለት ባደጉ ሀገራት በፍ/ቤት ውሳኔዎች የዳበረ ጁሪስፕሩደንስ ፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ Google የsearch engine ሲሆን በዚህ ምልክት ጫማ ቢመረት እና ገበያ ላይ ቢውል የዚህን search engine distinctive ባኅርይ የሚያደበዝዘው በመሆኑ ጥበቃ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡ distinctive ባኅርይን dilute የሚያደርጉ ወይም blurring effect የሚያሳድሩ ከሆነ ለተመሳሳይ ዓይነት ምርትና አገልግሎት ባይሆን እንኳ ለታዋቂ ምልክቶች ጥበቃ ይሰጣል፡፡ የዚህ ዋና ዓላማም የንግድ ምልክት ከምርትና አገልግሎት ጋር ቁርኝትን የሚፈጥር እና ምልክቱን ስናይ በፍጥነት ወደ አእምሯችን የሚመጠው ይህ ታዋቂ ምርት

ወይም አገልግሎት በመሆኑ ይህን እውቅና dilute ወይም blur የሚያደርጉ ከሆነ እንደ infringement የሚቆጠሩበት አግባብ አለ ብለዋል፡፡

ተዋቂ የንግድ ምልክቶች ጥበቃን በሀገራችንን ስንመለከት ኢትዮጵያ በየትኛውም የአለምአቀፍ የአእምሯዊ ንብረት ምብት ጥበቃ ስምምነት አባል አይደለችም፡፡ ታዋቂ የንግድ ምልክቶች በምርቱ ባህርይ እና የምርት አካባቢ የተለዩና distinctive መሆን አለባቸው ብለዋል፡፡ mcdonald በአለምአቀፍ ደረጃ የሚታወቅ የምግብ ሠንሠለት በሀገራችን ቅርንጫፍ የለውም ስለሆነም በዚህ የንግድ ምልክት ላይ የመብት ጥሰት ቢፈጠር የሀገራችን ፍ/ቤቶች እንዴት ነው የሚያዩት የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ሲሆን በታዋቂ የንግድ ምልክቶችን የመንለይበት ጋይድላይን ወይም የፍርድ ቤት ልምድ የለንም ብለዋል፡፡ በሌሎች ሀገራት አንድ የንግድ ምልክት ታዋቂ መሆን አለመሆኑ የሚለዩት የተለያዩ መሣሪያዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸው፡፡

1. የሽያጭ መጠንና የገበያ ድርሻ፤
2. የተጠቃሚዎች ብዛት፤
3. በሚመለከታቸው አካላት ወይም ዘርፎች ታዋቂ መሆን፤
4. ታዋቂ ስለመሆኑ ዳሰሳ በማድረግ፤
5. ማስታወቂያዎቹ ወዘተ ናቸው፡፡

በሀገራችን ግን ይህ ዓይነት ነገር አልተለመደም፡፡

በሦስተኛ ወገን መብት ምክንያት የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ ከሚከለክሉ ምክንያቶች አንዱ አንድ የንግድ ምልክት በማይመዘገብ እንኳ ረዘም ላለ ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል እውቅና ያተረፈ እንደሆነ ሕጉ ላይ የተመለከተ ሲሆን የአዋጁ አንቀፅ 7 (2) እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

*የንግድ ምልክቱ አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይ የሆኑ የሌላ ሰው እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በሚመለከት በሚገባ ከሚታወቅ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ግልጋሎት ላይ ከዋለ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት ወይም ሊያሳስት በሚችል ደረጃ ተመሳሳይ ከሆነ ወይም ትርጉሙን ከያዘ፤*

የሚል ሲሆን ለምሳሌ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እስካሁን የንግድ ምልክቱን ያላስመዘገበ ሲሆን ምልክቱ ግን በግልጋሎት ምክንያት ጥቅም ላይ በመዋሉ ጥበቃ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ጥቅም ላይ መዋል የሚለው ሐርግ አሁንም ቢሆን ግልፅ አይደለም ብለዋል፡፡ ገላጭ የሆኑ የንግድ ምልክቶች የማይመዘገቡ ሲሆን ገላጭ ቢሆን እንኳ ረዘም ላለ ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋሉ መሠረት ጥበቃ ይሰጠዋል በምሳሌነትም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማንሳት ገለፃቸውን አጠናቀዋል፡፡

## <u>አቶ ቢኒያም ታፈሠ - አወያይ</u>

ጽሑፍ አቅራቢዋን አመስግነው የተወሰኑ ጥያቄዎችን አወያዩ ያነሱ ሲሆን ታዋቂ የንግድ ምልክቶችን በተመለከተ ምን ዓይነት ስምምነቶች አሉን፣ በኛ ሀገር ያለው ሁኔታስ ምን ይመስላል፤ የኛ ሀገር ሕግ ታዋቂ የንግድ ምልክቶች የሚሰጠው ልዩ ጥበቃ በምን ሁኔታ እንደሆነ ገለፃው የዳሠሰ መሆኑን አስታውሰው አንድ መሠረታዊ ጥያቄ ያነሱ ሲሆን ይህን የንግድ ምዝገባ አዋጁ አንድ የንግድ ስም በውጭ ሀገር የተመዘገበ እንደሆነ በሀገር ውስጥ እንዳይመዘገብ ገደብ የሚያደርግ ሲሆን የንግድ ምልክት ምዝገባን በሚመለከት በውጭ ሀገር የተመዘገበ ምልከት ታዋቂ ካልሆነ በሀገር ውስጥ ሊመዘገብ የሚችል መሆኑ የተቀመጠ ሲሆን ይህን ልዩነት እንዴት ታዩታላችሁ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

ታዋቂ የንግድ ምልክቶች የሚባሉት ለምሳሌ N/B, Safeway, yahoo, cocacola, marriot, in and out, ወዘተ ጠቅሰው በኛ ሀገር እንደ መንግሥት የቴክኖሊጂ አዳፕቴሽን የተፈቀደ ሲሆን የንግድ ምልክትን መኮረጅ ግን አግባብ እንዳልሆነ ይልቁኑ የሀገራችንን ማርክ ይዘው እጅግ ስኬታማ የሆኑ የንግድ ሰዎች መኖራቸውን በመጠቆም መድረኩን ለጥያቄ እና ሀሳብ አስተያየት ለተሳታፊው ክፍት አድርገዋል፡፡

Microsoft Coca-Cola DANGOTE

<u>አቶ ኢሣያስ ይርጋ - ጠበቃ</u>

በፌደራል ሰበር ሰሚው ችሎት ከተወሰኑ መዛግብት መካከል በቅፅ 12 ላይ የorion ማስቲካ የንግድ ምልክት በኢትዮጵያ ያልተመዘገበ ነገር ግን በውጭ ሀገር የተመዘገበ ሲሆን አንድ ሰው "O" የሚለውን ፊደል ወደ "Q" የተቀየረ ማስቲካ ከውጭ ሀገር ሲያስመጣ የነበረ ሰው በስር ፍ/ቤት በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሲሆን የሰበር ችሎቱ እንኳ ወንጀል አይደለም በሚል ሳይሆን በአዋጁ (1998) መሠረት የንግድ ምልክቱ በድጋሚ አልተመዘገበም በሚል ነው ነፃ የተባለው ካሉ በኋላ ይሄ ትክክል እንዳልሆነ ጠቁመው በዚህ ረገድ የጽሑፍ አቅራቢዎችን አስተያየት ጠይቀዋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ የethio-cement የሰበር ችሎቱ የማሳከር ሁኔታ መኖርን መሠረት አድርጎ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይም እንዲሁ ሃሳብ ቢቀርብበት ካሉ በኋላ የወንጀል ጉዳዮችም ቢዳሰሱ ትሩ እንደነበረ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

<u>አቶ ታረቀኝ ሞላ - ጠበቃ</u>

የቀረበው ጽሑፍ እጅግ በጣም ጥሩ እንደነበረ ገልፀው የፕሮጀክተሩ አለመስራት ታዋቂ የንግድ ምልክቶችን እንዳናያቸው ምክንያት ሆኖ እንደነበር ገልፀዋል፡፡

<u>አቶ መታሰቢያ ኃይሉ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

የቀረበው ገለፃ በጣም ጥሩ እንደሆነ ከጠቆሙ በኋላ ከጠበቆች ምን ይጠበቃል የሚለው በገለፃው ውስጥ ቢካተት መልካም እንደነበር አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

<u>አቶ ዮሴፍ አዕምሮ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ</u>

የቀረበው ገለፃ ጥሩ እንደሆነ ገልፀው የታወቁ የንግድ ምልክቶች መጠበቅ አለብን የሚል ነገር የቀረበ ስለመሆኑ አውስተው እነዚህን ምልክቶች በመጠበቅ ሀገራችን ልታገኝ የምትችለው ጥቅም ምን እንደሆነ የጠየቁ ሲሆን የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ የተባለውን በተመለከተ

ለምልክቶቹ ጥበቃ በመስጠት ኢንቨስትመንት መሳብ ይቻላል? ምንስ እናገኛለን? ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>**አቶ ንጉስ ዓለሙ - ከኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ**</u>

ገለፃው እጅግ በጣም ጥሩ ነው ካሉ በኋላ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የንግድ ምልክት እንዳይመዘገብ የተደረገበት አግባብ የተገለፀ ሲሆን የአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካለመመዝገብ ባሻገር እንዳይጠቀም የማድረግ ወይም አንድ የንግድ ምልክት ጥቅም ላይ እንዳይውል የመከልከል ሥልጣን የለውም ወይ? ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

<u>**አቶ በላይ መሸሻ - ጠበቃና የሕግ አማካሪ**</u>

የንግድ ምልክት ገላጭ መሆን እንደማይችልና ገላጭ ከሆነ የማይመዘገብ ስለመሆኑ የተቀመጠ ሲሆን Commercial Bank of Ethiopia የሚለውገላጭ ነው ባይመዘገብም ብዙ ጊዜ በመጠቀሙ ምክንያት ጥበቃ ይሰጠዋል ተብሏል ይሁን እንጂ ሌላ አካል ይህን ሊያስመዘግብ ሲመጣ ምን ይደረጋል? በማለት የጠየቁ ሲሆን አወያዩ ከሻይ እረፍት በፊት ያነሱት የመወያያ ጥያቄን አስመልክቶ የንግድ ምልክት ጥበቃ ከንግድ ስም ጋር የተለያየ የትበቃ ቅድመሁኔታ ስለተሰጠበት ምክንያት የጠየቁ መሆኑን አስታውሰው በጥያቄው ላይ ያላቸውን ሃሳብ የገለፁ ሲሆን ንግድ ምልክት የቅንጦት ሲሆን የንግድ ስም ግን ግዴታ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተለየ ጥበቃ ተችሮታል ብለዋል፡፡

<u>**አቶ ተመስገን --------------------**</u>

“Descriptive” የሚባለው extent ምንያህል ነው? ለምሳሌ Fair view realstate ለማስመዝገብ ተሞክሮ ገላጭ ነው በሚል ሳይመዘገብ ቀርቷል፡፡ መዝጋቢው አካል ጋር ሰፊ discretion ነው ያለው ሚሰጠውም ማብራሪያ የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ምን ያህል ድረስ ይሄዳል ገላጭ የሚለው? በማለት ጥያቄቸውን የቀጠሉ ሲሆን በኛ ሀገር በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በፍትኃብሔር ነፃ የሚባልበት ሁኔታ አለ፡፡ የአእምሯዊ ንብረት በትክክልም ንብረት ከሆነ ጠንከር ያለ ጥበቃ ያሻዋል ያሉት አቶ ተመስገን ለንግድ ምልክት ጥበቃ መስጠት ቀጥታ የውጭ ኢንቨስትመንትን ከመሳብ ብቻ መቃኘት እንደሌለበት ይልቁኑ ጥበቃውን መስጠት የመልካም ሥነምግባር ጉዳይ እንደሆነ የሌላን ንግድ ምልክት መውሰድ ስርቆት እንደሆነ አበክረው ገልፀዋል፡፡

## አቶ ፋሲል ስለሺ ጠበቃና የሕግ አማካሪ

አቶ ዮሴፍ ያነሱት ጥያቄ መሠረታዊ እንደሆነ አስታውሰው ኮፒ የማድረግ አቅም ያላቸው የደቡብ ምስራቅ ኢሲያ ሀገራት ኮፒ በማድረግ ተሰማርተው ሳለ የእኛ ሀገር ኮፒ ብታደርግ ችግር የለውም ብዬ ነው የማምነው ካሉ በኋላ በሚገባ ጥቅም ላይ ሲውል የነበረ የንግድ ምልክትን አንድ ሌላ ሰው ሊያስመዘግብ ቢመጣና ግጭት ቢፈጠር እንዴት ነው የሚፈታው? ብለው የጠየቁ ሲሆን የፓሪስ ስምምነትን በመፈረም አባል ሀገር በመሆን የምናገኘው ጠቀሜታ ምንድነው? ብለዋል፡፡

## አቶ ጌትነት ያውቃል - ጠበቃ እና የአእምሯዊ ንብረት ኤጀንት

የአእምሯዊ ንብረት መብት ጥሰት የሚጀምረው ቀድሞ በማስመዝገብ ነው ያሉት አቶ ጌትነት counterfeit ማድረግ በውጭ ሀገራት ሰዎችም የሚፈፀም መሆኑን እና ቀደም ብሎ በነበረው ሕግና አሠራር መሠረት የንግድ ምልክቱን ለማስመዝገብ ከውጭ የሚመጣው ሰው home certificate ወይንም በሀገሩ በንግድ ምልክትነት ያስመዘገበበት ሰነድ የሚጠየቅ ነበረ ሲሆን አሁን ግን business incorporation certificate ኮፒ ነው የሚጠየቀው ፅ/ቤቱ በራሱ ተነሳሽነት ነው authenticate እንዲደረግ የሚያደርገው፡፡ በዚህ ምክንያት የውጭ ሀገርን በሚመለከት ሕጉ ክፍተት ያለበት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡



**<u>ወ/ሮ ልደት አበበ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>**

የorion ማስቲካ well-known ነው አዋጁ ከመውጣቱ ማለትም 1998 ዓ.ም. በፊት ኢተዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ እንደነበረ በወቅቱም ጥቅም ላይ ሲውል የነበረው የdeposit system እንደነበረ አስታውሰው በአዋጁ መሠረት ለድጋሚ ምዝገባ የ18 ወር የጊዜ ገደብ የሰጠ ይሁን እንጂ ይህን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ግን ከአዋጁ በኋላ 6 ዓመት ቆይቶ ነው ያሉት ወ/ሮ ልደት orion በድጋሚ አልተመዘገበም፡፡ ይህም ሆኖ ፍ/ቤቱ መዝገቡን የወሰነበት አግባብ ትክክል እንዳልሆነ በአቋማቸው አንፀባርቀዋል፡፡

የethiocement ጉዳይ በunfair competition የቀረበ ክስ ሲሆን ሌላ ሰው ኢትዮ-ሲመንት በሚለው ላይ 5 ስታር ጨምሮ የንግድ ምልክት ይዞ የመጣ ሲሆን ቀደም ብሎ ጥቅም ላይ ሲውል የነበረው ኢትዮ-ሲመንት የንግድ ስም በምርቱ ፓኬጂንግ ላይ ስሙን የሚፅፍና በሕዝቡም የሚታወቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ኢትዮ-ሲመንት ላይ 5 ስታርን መመዝገብ በማህበረሰቡ ዘንድ መሳከር (confusion) ይፈጥራል በሚል ምክንያት ሳይመዘገብ ቀርቷል በunfair competition ሕግ መሠረት ነው ብለዋል፡፡

**<u>አቶ ቢኒያም ታፈሠ - አወያይ</u>**

የእኛ ፍ/ቤቶች ከአእምሯዊ ንብረት መብት ሕጎች የራቁ ናቸው በማለት የጀመሩ ሲሆን የorion'ን በተመለከተ የ1998 አዋጅ የ18 ወር ድጋሚ ምዝገባ ይላል ይሁን እንጂ የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት ከ6 ዓመት በኋላ የጀመረ ይሁን እንጂ የድጋሚ ምዝገባ ሥርዓት ከ6 ዓመት በኋላ የጀመረ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ግን በ18 ወር አልተመዘገበም በሚል ችሎቱ ከእውነታው ሙሉ ለሙሉ የተራራቁ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የኢትዮ ሲመንትም ከዚህ የሚለይ አይደለም ብለዋል፡፡

**<u>ወ/ሮ ልደት አበበ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>**

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የንግድ ምልክትን አስመልክቶ አንድ ቤተክርስቲያን በመቃወሙ ምክንያት ሳይመዘገብ ቀርቷል ነገር ግን የአእምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ግን እንዳይጠቀም መከልከል አይችልም ቅሬታ ያለው ወገን ነው ይህን ማድረግ የሚችለው በመጠቀም የንግድ ምልክት ጥበቃ እንዲቸረው ሊደረግ ይችላል፡፡ የንግድ ምልክት ጥበቃ ዋና ዓላማ መሳከርና መደናገርን ለማጥፋት ነው፡፡ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚሰጠው ከሌሎች የሚለየው ነገር ሲኖር

እንደሆነና ገላጭ የሆኑ ቃላትን ወይም ምልክቶችን ማስመዝገብ የማይቻል መሆኑን ገልፀው የዚህ ምክንያትም ገላጭ የሆኑ ቃላትና ምልክቶችን በሞኖፖሊ መያዝ አግባብ ባለመሆኑ ሲሆን ረዘም ለሚል ጊዜ ገላጭ የንግድ ምልክቶችን በመጠቀም ጥበቃ ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የdescriptive ትርጓሜ አድማስ ምን ድረስ ነው የሚለው ሁልጊዜም አከራካሪ ነው፡፡ በሕጉ ላይ ለቃሉ ትርጓሜ የተሰጠ ሲሆን ምርቱ የመነጭበት ቦታ፣ የዕቃው ጥቅም ወዘተ የሚገልፁ ቃላት ወይም ምልክቶችን በንግድ ምልክትነት ማስመዝገብ የማይቻል ሲሆን ለምዝገባ ቅድመሁኔታዎችን በልማድ ማዳበር ወይም በመመሪያና ጋይድላይን መወሰንና ገደብ ማበጀት ተገቢ እንደሆነ ጠቁመው ይህ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በአእምሯዊ ንብረት መብት ጥበቃ የሰለጠኑ ሀገራትም በዚህ ረገድ የሚቸገሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የFair View Realstate ጉዳይም ምንም ዓይነት መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት እንደመዘጋቢው ግምገማና ምርመራ የሚመሰረት እና ከጉዳይ ጉዳይ የሚለያይ መሆኑን ገልፀው ሌሎች ሀገራት የአእምሯዊ ንብረት ችሎት (bench) ያለ ሲሆን  በኛ ሀገር በፖሊስ፣ በፍርድ ቤት እንዲሁም በገቢዎችና ጉምሩክ አካባቢም የዚህ መብት እውቅና ዝቅተኛ ነው፡፡

በኛ ሀገር ሕግ መሠረት የንግድ ምልክት ጥበቃ እንዲያገኝ ማስመዝገብ እንደቅድመሁኔታ የተቀመጠ ሲሆን በልማድ ለረዥም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ምልክት ጥበቃ የሚሰጠው ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌዎች በተቃራኒ ንባብ (accontrario reading of Art 7) መረዳት ይቻላል፡፡ በሁለቱ መካከል ግጭት ቢፈጠር የትኛው ተቀባይነት ይኖረዋል የሚለውን በተመለከተ ሕጉ poor drafting ይታይበታል ያሉት ወ/ሮ ልደት የቀደመና የተሻለ መብት ያለው prevail ያደርጋል በማለት አንድ የንግድ ምልክት ከተመዘገበ በኋላ የcancellation ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

የሀገር ውስጥ የንግድ ምልክት የሚጠይቀው business license አንዱ መስፈርት ሲሆን የውጭ ሀገር የንግድ ምልክት ለመመዘገብ ቀደም ብሎ home certificate እንዲመጣ ይደረግ እንደነበር አስታውሰው ሕጉ ከወጣ በኋላ ግን business incorporation certificate ማምጣት ብቻ በቂ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት ታዋቂ የሆኑ የንግድ ምልክቶች በኢትዮጵያ ያልተመዘገቡ በመሆናቸው በሕንድ ወይም በቻይና ያለ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ የራሱ አድርጎ የሚያስመዘግብበት ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የሕጉ ዓላማ ግን ከውጭ የሚመጡ ኢንቬስተሮች ቀለል ባለ ሥነሥርዓትና በተመቻቸ ሁኔታ ለማስተናገድ በሚል ቅድመሁኔታዎቹ እንዳይበዙ የተደረገ እንደሆነ ጠቁመው ይህ ማለት ግን ቅሬታና ተቃውሞ ካለ አይታይም

ማለት እንዳልሆነ ገልፀው በውጭ ሀገራት የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ምንም ቅድመሁኔታ እንደሌለ ለአብነትም ፈረንሳይን ጠቅሰዋል፡፡

## አቶ ቢኒያም ታፈሠ - አወያይ

የንግድ ምልክት ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች የሚለይ መሆኑን ጠቁመው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ካለው ነባራዊ ሁኔታ ቴክኖሎጂዎችን እየኮረጁ ለማህበረሰቡ ፍጆታ እንዲውሉ ማድረግ ላይ ችግር እንደሌለባቸው ገልፀው የንግድ ምልክት ከመፍጠር አንፃር ግን አቅም ያንሰናል የሚል እምነት የለኝም ብላዋል፡፡ የተወሰኑ ምሳሌዎችን የጠቀሱት አቶ ቢኒያም ጀነራል ኤሌክትሪክ የተባለ የቦይንግን ጨምሮ የተለያዩ ማሽነሪዎች ኢንጅን የሚሰራ ተቋም በመንግሥት ተጋብዞ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ መጥቶ ሊያስመዘግብ ሲል ፒያሳ አካባቢ በተመሳሳይ ስም ቀደም ብሎ አስመዝግቦ ሲሰራበት የነበረ ሾፕ በመኖሩ ምክንያት መስተጓጎል ገጥሞ የነበረ ቢሆን የንግድ ሚኒስቴር ጉዳዩን በአግባቡ አይቶ እልባት የሰጠበትን ጉዳይ ጠቁመው ኢንቨስትመንት ማለት capital inflow ብቻ ሳይሆን technology transfer ጭምር እንደሆነ በመግለፅ ታዋቂ የንግድ ምልክቶችን መጠበቅ እንደሚገባና መኮረጅ እንደማያስፈልግ በአቋማቸው አንፀባርቀዋል፡፡

በዓለምአቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሚባሉት የንግድ ምልክቶች እንደ ኮካኮላ፣ ሳምሰንግ፣ ማይክሮሶፍት፣ ያሆ፣ ጉግል ወዘተ እንደሆኑ ከሀገር ውስጥ ደግሞ እንደ ኢቲቪ፣ አዲስ ሻይ፣ ኮዳክ ወዘተ የጠቀሱ ሲሆን የንግድ ምልክት descriptive መሆን የለበትም ነገር ግን suggestive ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል ብለዋል፡፡

## ወ/ሮ ልደት አበበ - ጽሑፍ አቅራቢ

የፓሪስ ኮንቬንሽን አባል እንሁን ወይስ ይቅርብን የሚለውን ጭብጥ አስመልክቶ በዚህ ውይይትና በዚህ መድረክ ልንወስነው የማንችለው ይልቁኑ ጥናቶችን የሚሻ እና ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ቁምነገሮች ማየትና መመርመር እንደሚገባ ጠቅሰዋል፡፡ የፓሪስን ስምምነት ብቻ ሳይሆን በሌሎች የዓለምአቀፍ ግዴታዎች ላይ ከመገባቱ በፊት ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ፣ የሌሎች መሠል ሀገራት ተሞክሮ እና ጥናት የሚፈልግ እንደሆነ ገልፀው እነዚህን ስምመነቶች ለመፈረም ጥረትና እንቅስቃሴ ስለመኖሩ የጠቀሱት ወ/ሮ ልደት አሜሪካ የበርን

ኮንቬንሽንን ሳትፈርም ዘለግ ላለ ጊዜ የቆየችው የእንግሊዝ መፅሃፍትን የሚጠቀሙ በመሆናቸው እንደሆነ በምሳሌ በማስደገፍ አብራርተዋል፡፡

<u>**አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢ/ሕ/ባ/ማኅበር ፕሬዝዳንት**</u>

በውይይት መድረኩ ላይ ጽሑፍ በማቅረብና ፕሮግራሙን ስፖንሰር በማድረግ ብቸኛ ሴት ለሆኑት ወ/ሮ ልደት አበበ ያላቸውን ምስጋና አቅርበው፣ መድረኩን በአወያይነት ሲመሩና ተጨማሪ ሃሳብ በመሰንዘር በአወያይነት ተሳታፊ ለሆኑት አቶ ቢኒያም ታፈሠ እንዲሁም በመወያያ መድረኩ ለተገኙ ተሳታፊዎች፣ ሃሳብ አስተያየታቸውን ለሰጡ ታዳሚዎች በሙሉ ያላቸውን ክብር በመግለፅ ምስጋና አቅርበው ውይይቱ ከቀኑ 7፡00 ላይ ተጠናቋል፡፡

---